# ልጆችና ተግሳጽ፡- የልጆች መመሪያ

ልጆች የሚወለዱት መልካም ምግባር ምን እንደሆነ ተምረው አይደለም። ከወላጆቻቸውና ከሌሎች እንክብካቤ ሰጪዎች መማር ያስፈልጋቸዋል። ወላጆችም ቢሆኑ ይህን ማድረግ ሁልጊዜ ቀላል ስራ እንዳልሆነ ይገነዘባሉ።

## <u>በየትኛው ዕድሜ ላይ ምን ዓይነት ባሕርይ ማሳየት እንደሚጠበቅ ማወቅ</u>

የኩሽና ዕቃ ማስቀመጫውን ከፍቶ ውስጥ ያለውን ሰሃን ሁሉ እያነሱ ኩሽናው ወለል ላይ መከስከስ ለአንድ የሁለት ዓመት ልጅ እንደ ብልግና የሚቆጠር ነገር ላይሆን ይችላል። ይህ ልጅ ወይም ይህች ልጅ ስለ አካባቢያቸው እየተማሩ ነው ማለት ነው። የአራት ዓመት ልጆች ከወንድሞቻቸውና ከእህቶቻቸው ጋር መደባደባቸው የተለመደ ነገር ሊሆን ይችላል። ተመሳሰይ ዕድሜ ላይ ያሉ ልጆች ካሉአቸው ወላጆች ጋር መነጋገር በየትኛው ዕድሜ ላይ የሚያሳዩት የትኛው ባሕርይ ጤናማ መሆኑን ለመገንዘብ ይረዳል። አንዳንድ ወላጆች ሌሎች ልጆችም በዚያ ዕድሜ ተመሳሳይ ባሕርይ እንደሚያሳዩ ሲያውቁ እፎይታ ይሰማቸዋል።

## <u>ምሳሌ በመሆን አስተምሯቸው</u>

ልጆች የሚማሩት ሌሎችን በመኮረጅ ነው። ወላጆች መልካም ምሳሌ መሆን ያለባቸው ለዚህ ነው። እኛ ወላጆች ለልጆቻችን አክብሮት ማሳየታችን በጣም አስፈላጊ ነው። ሌሎች አክብሮት የሚያሳዩአቸው ከሆነ ልጆች ራሳቸው ሌሎችን ያከብራሉ። ልጆች ለየት ያሉ መሆናቸውን ማወቅ ቢያስፈለጋቸውም የአንድ ቡድን አካል እንደሆኑ እንዲሰማቸውም ማድረግ ያስፈልጋል። ያላቸውን ማካፈልን ማዳመጥንና በየተራ አንዳንድ ነገሮችን መሥራትን የምናስተምራቸውም ለዚህ ነው

## <u>ምን እንደምትናገሩና እንዴት እንደምትናገሩ አስቡበት</u>

ከልጆቻችሁ ጋር የምትነጋገሩት ሌሎች ሰዎች እናንተን እንዲያነጋግሩአችሁ በምትፈልጉበት የድምጽ ቃና መሆን አለበት። ከእነርሱ ጋር ስትነጋገሩም ሆነ ስለ እነርሱ ስትናገሩ አክብሮት ባለበት መንገድ ይሁን። አን ሁልጊዜ ባለጌ ነች ወይም ዮሴፍ ሁልጊዜ ሰነፍ ነወ የሚሉ ዓይነት አነጋገሮችን አስወግዱ። ሁልጊዜ የልጆቹን ደካማ ጎን መጥቀስ አንድ ቀን እንዲያሻሽሉ ያደርጋቸዋል ብሎ በማሰብ ልጆችን መንቀፍ ቀላል መስሉ ሊታይ ይችላል። ሆኖም ይህ ብዙውን ጊዜ ውጤቱ የተገላቢጦሽ ነው። ልጆች ትኩረት የሚያገውት ወላጆቻቸወ የማይወዱትን ነገር በማድረግ እንደሆነ ሊሰማቸው ይችላል።

የተሻለ ባሕርይ እንዲያሳዩ ማበረታታት የሚቻልበት የተሻለው መንገድ በተቻለ መጠን እነርሱን በማመስገን ሲሆን በትናንሽ ነገሮች ይህንን ማድረግ ይቻላል። ለምሳሌ ያህል አን ዛሬ በጣም ረድታኛለች። አሻንጉሊቶቿን በሙሉ በቦታዋ የመለሰችው እራሷ ነች ማለት ይቻላል። ይህ ማለት ልጆች ጥፋት ሲፈጽሙ ፈጽሞ ሊወቀሱ አይገባም ማለት አይደለም። ሆኖም የሚወገዘው ልጁ ራሱ ሳይሆን መጥፎ ባሕርይው መሆን ይኖርበታል። አንተ በጣም ባለጌ ልጅ ነህ ከማለት ይልቅ አሁን ያደረግከውን አልወደድኩትም ወይም እኔ እንዲህ ዓይነት ባሕርይ እንዲኖርህ አልፈልግም ለማለት ሞክሩ።

## ገደብ አበጁ

ልጆች ምን ዓይነት ባሕርይ እንዲያሳዩ እንደሚፈቀድላቸውና ምን ዓይነት ባሕርይ እንደማይፈቀድላቸው እንዲያውቁ አድርጉ። ግልጽ ገደብ አበጁ። ደህንነት እንዲሰማቸው አድርጉ። ተቀባይነት ያለውና የሌለው ነገር ምን ስለመሆኑ ያላችሁ አቋም ወጥ እንጂ የሚቀያየር መሆን የለበትም።

## አንዳንድ ጊዜ ልጁ ያለውን አይሆንም የማለት መብት አክብሩለት

እነዚህ ልጁን ብቻ የሚመለከቱ ውሳኔዎች ሊሆኑ ይችላሉ። ለምሳሌ የትኛውን ልብስ መልበስ እንደሚፈግ የሚያደርገው ውሳኔ አንዱ ነው። ልጆች አይሆንም ማለትን መማራቸው ጥሩ እንደሆነ አስታውሱ። ለምሳሌ ያህል ፀጉረ ልውጥ ለሆኑ ሰዎች አይሆንም ማቁታቸው ለደህንነታቸው ከሁሉ የተሻለው ነገር ነው።

## ልጆች ሲተባበሩአችሁ እቅፍ እድርጋችሁ አመስግኗቸው

ይህ ጥሩ ባሕርይ እንዲያሳዩ ያበረታታቸዋል

## ልጆች ማድረግ ከሚችሉት ነገር በላይ አትጠብቁባቸው

አንድ የአምስት ዓመት ልጅ በሐኪም ቤት ተራ መጠበቂያ ቦታ አርፎ እንዲቀመጥ የሚጠበቅበት ቢሆንም የሁለት ዓመት ልጅ ይህንን እንዲያደርግ ልትጠብቁበት አትችሉም። ታጋሽ ሁኑ። የልጁን ዕድሜ ከግምት ውስጥ አስገቡ

## ልጆችን ከመምታት ተቆጠቡ

ይህ ሌሎችን ለበቆጣጠር የተሻለው መንገድ ኃይል እንደሆነ እንዲሰማቸውና የሚያደርግና እነርሱም ሌሎችን ልጆች እንዲመቱ የሚያበረታታ ይሆናል

The material in this brochure has been adapted from documented by NSW Multicultural Health Communication Service.
This brochure can be reproduced as required.

Canadian Mental Health Association – Edmonton Region Phone: (780) 414.6300 www.cmha-edmonton.ab.ca
Edmonton Mennonite Centre for Newcomers Phone: (780) 424.7709 www.emcn.ab.ca
Multicultural Health Brokers Co-op Phone: (780) 423.1973